Amhari

# የእጅ አሻራ ያለብን ሰዎች ዲፖርቴስሽንን እንዴት እንከላከላለን?




last update
July 2018

## *_መግቢያ_*

እጅህን አውሮፖ ሁብረት ከሆኑት ለአንዱ አገር ሰጠህ ከሆነ ለምሳሌ ጣሊያን ቡልጋሪያ ሀንጋሪ ወይንም ግሪክ ሊህን
ይችላል በነዚህ በአውሮፓ ሁብረት አገሮች አልፉህ ወይንም ጥገኝነት ጠይቀህ ሊሆን ይችላል ሆኖም ግን
ጥገኝነትህ ዋጋ
አጥቶ ወይንም ጥገኝነት ሳትጠይቅ ወደ ሌላ አውሮፓ አገር ጥገኝነት ብትጠይቅ ጥገኝነትህ ውድቅ ሆኖ መጀመሪያ ወደ
ጠየቅህበት ወይም በአለፍህበት አገር ትመለሳሉህ ይህ የአውሮፓ ሁብረት ዩዱብሊን ህግ ነው
ወደ ቀድሞው እጅ ወደሰጠህበት አትመለስም ብትባል ሙሉ ለሙሉ መኖር ተፈቀደልህ ማለት አይደለም ግን
የጥገኝነት ጥያቄህ እዚህ አገር መታየት ይጀምራል ማለት ነው
በመጀመርያ ሁላችንም ራሳችንን አደራጅተን ትክክለኛውን መንገድና መሆን የሚገባውን ማድረግ ይገባናል
ዲፖርቴሽን በአንዳንድ አገሮች (ጣላያን ሀንጋሪ ቡልጋሪያ ማልታ)የመሳሰሉትን የጀርመን ፍርድ ቤት መመለስ
የለባቸውም በሚል ክርክር ላይ ይገኛሉ በተለይ ቤተሠብን በተመለከተ ከፍተኛ የጤና ችግር ያለው ከሆነ በጠበቃ
በመታገዝ መመለሱን ማስቀረት ይቻላል
አሻራ ኖሮህ ወደ መጀመሪያ በአለፍህበት (እጅ በሰጠህበት )አገር ሊመልሱህ ቢሞክሩ የተለያየ መንገዶችን
ተጠቅመህ አለመመለስ ትችላለህ እነዚህ መንገዶች ከዚህ በታች አሉልህ ተመልከቷቸው

## *_ማስታወሻዎች _*

ሁለት አይነት የእጅ አሻራ አለ
1/ አንድ አገር እንደገባህ የሚሰጥ አሻራ
2/ጥገኝነት በመጠየቅ የሚሰጥ አሻራ
በነዚህ በሁለቱ ምክንያት ወደ ሌላ አገር ጥገኝነት ስትጠይቅ ጥገኝነትህ ውድቅ ይሆናል ስለዚህ ጥገኝነትህ ውድቅ
እንዳሆን የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ማስቆም ይቻላል

## *_የዱብሊን ህግ እንዴት ይ_*ሰራል

የአንድን ሰው አሻራ ለማወቅ የመጣህበትን መንገድ በመጠየቅና የእጅህን አሻራ በመውሰድ በቀላሉ መጀመሪያ
የሰጠህበትን አገር ማወቅ ይቻላል ከዚያም በአውሮፓ ሁብረት ህግ ስምምነትመሰረት ወደ መጀመሪያ ወደሰጠህበት አገር
ትመለሳለህ ለመመለስ መጀመሪያ የሰጠህበትን አገር እንዲቀበል ትዛዝ ይተላለፍል
መጀመሪያ የሰጠህበት አገር ለመቀበል በ6ወር ግዜ ፈቃደኛ ካልሆነ ጉዳይህ እዚህ መታየት ይጀምራል

## *_ጠቃሚ_* ነጥብ

የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብተህ በፍርድ ቤት ለመታየት 6ወር ግዜ ሊወስድ ይችላል በዚህ በ6ወር ግዜ ካልተቀበሉህ
እንደገና ወደ ፍርድ ቤት ሄደህ ማመልከት ትችላለህ አሁንም ካልተቀበሉህ የ6ወርግዜ አገር ለቀህ የምትወጣ መሆኑን
ይፃፍልሀል በዚ ግዜ ፖሊሶች ሲመጡ ራስህን ከደበቅህ 6ወሩ ወደ 18ወር ያድጋል አንተን የማደኛ ግዜ ይጨመራል

## *ከ18አመት*_በታች የሆኑና ለመመለስ የተቸገሩ

ከ18 አመት በታች የሆኑ በአንድ አገር ተወስነው መቀመጥ አይችሉም ስለዚህ በተለያየ ግዜ ለተለያዩ
የአውሮፓ
አገሮች ጥገኝነት መጠየቅ ይችላሉ ምክንያቱም መጀመሪያ ከሰጡበት አገር ወረቀት ካልተቀበሉ
መጀመሪያ የሰጡበት አገር በውሸት እድሜያቸውን ጨምረው ከሰጡ ጀርመን የጥገኝነት ጥያቄዎን ማየት ይችላል
ይህ አይነት
አሰራር በሁሉም አውሮጳውያን አገር አይሰራም



## በዱብሊን ምክንያት እንዳንመለስ የሚያደርጉት *_ምክንያቶች_*

*1/ራስን ማጠንከርና የተለያዩ የዱብሊን የህግ ባለሙያዎች ዶክተሮች ወይንም የስነ ልቦና ባለሙያዎችን
ድጋፍ መጠቀም*

*2/ ሌላው በጣሊያን በሀንጋሪ በቡልጋሪያ ስትኖር የአኖኗር ችግሮችን ዘርዘር ባለ መንገድ ለህግ ባለሙያ ማቅረብ
ያስፈልጋል*
* ለምሳሌ ያህል በነዚህ አገሮች *
* :ታስራችሁና ተደብባችሁ ከሆነ*
* : በቂ ምግብ ካለገኛችሁ*
* : በቂ መጠለያ ቤት ከለላችሁ*
* : በቂ ህክምና አገልግሎቶች ካላገኛችሁ*
* የመሳሰሉትን ዶክመንትድ በሆነ መንገድ ማቅረብ አለባችሁ*

3*/ጀርምን ከደረሳችሁ በኃላ ሊረዷችሁ የሚችሉ ድርጅቶችን ወይንም ግለሰቦችን መገኘት አለባችሁ በተለይ የዱብሊን
ህግ የሚያውቅ ጠበቃ መያዝ ግድ ይላል*

* ከዚህ በታች የአሉትን ሊንክ በመጠቀም የምክር አገልግሎቶች ታገኛላችሁ*
* http://w2eu.info/germany.en/articles/germany-deportation.en.html*
* https://www.youtube.com/watch?v=g2Umb7MyDhw&feature=youtube*
* http.//nodeportation.antira.info/abschiebungen-verhindern/

*4/ጠበቃ በመያዝጉዳይህን ፍርድ ቤት መውሰድ በተለይ በዱብሊን ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ጠበቆች በመያዝ ጉዳይህ
ጀርመን እንዲታይ ያደርገዋል*

*5/ከፍተኛ የጤና ችግር ካለብህ ለዶክተር ወይንምለስነ ልቦና ባለሙያ ማማከር በተጨማሪም ልጆች አባት አብሯችው
ከሌለ እናት ረዳት ስለሌት በሚል እዚሁ እንዲታይ ይደረጋል*

*6/ ፍርድ ቤቱጥያቄህን ውድቅ ቢያደርጉው የተለያዩ መንገዶች አሉህወደመጣህበት ላለመለስ*
* a/ ራስን በቡድን በማደራጀትፖሊስ ለመውሰድ ሲመጣ በትብብር ፖሊስን በመከላከል ለማስቀረት
  መምከር ይህ
  በአንድ ጀርመን ካምፕ የተሞከረ ነው ግን ፓሊስን ጉዳት ማድረስ አይቻልም*

  *b/ሁሉም የካምፑ ሰው ራሱን መደበቅ*

  *c/የሚፈለገውን ሰው ብቻ መደበቅ አያዋጣም ምክንያቱም ፖሊስ የማደኛ ግዜ ይጨመራል*

* _ማስታወሻ_*
*ራሳችንን መደበቅ አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ፓሊስ ማደኛግዜ ወደ \\ ወር ያራዝማል*
የቤተክርስቲያንጥገኝነት መጠየቅ ራስን ከፓሊስ መደበቅ ይቻላል በአካባቢው በሚገኝው ቤተክርስቲያኖች የአካባቢውን
ማህበረሰብ በመጠየቅ እንደጉዳያችሁ ቅደምተከተል የማግኘት እድል ይኖራቸዋል
የአምሮ በሽተኛ የእልብ ድካም የመስማት ችግር የመሳሰሉት ችግር ያለበት ሰው ከአኪም ወረቀት በማምጣት ጉዳዩ
ጀርመን እንዲታይ ይደረጋል

* ማስታወሻ*_
* ይጠየቅህው የጥገኝነት ጥያቄ ግዜ ከወሰደ የተሻለ ይሆናል ምክንያቱም የመመለሻ ግዜው ስለሚቃጠል ስለዚህ ጠበቃ
ማማከር ይጠበቅብሀል*

* መልካም እድል ይግጠምህ*

## ህጋዊ መንገድ በመጠቀም(ጠበቃ) በመያዝ ዲፓርቴሽንን ማስቆም ይቻላል

መመለስ ካልፈለጋችሁ የፊደራል መስሪያቤቱን በማሳመን በጀርመን የጥገኝነት መጠየቂያ ህግ መሰረተ መጠቀም ትችላላችሁ ሆኖም ግን አስቸጋሪ ነው:በአብዛኛው የጥገኝነት ጥያቄዎች ወደ ፍርድ ቤት በማመልከት የጥገኝነት ጥያቄዎችን ወደ ፊደራል የስደተኖች መስሪያቤቱ ጉዳዩን በማመልከት በጀርመን የጥገኝነት ጥያቄ መሰረት እንዲታይልን ጥያቄዎን ማቅረብ በመጀመሪያ መልሳችሁ ተቀባይነት ካላገኘ ትልቅ ቢጫ ፖስታ አገር ለቃችሁ እንድትወጡ የሚያስጠነቅቅ ይደርሳችኃል :

ትልቁ ቢጫ ደብዳቤ እንደደረሳችሁ ለአካባቢ አስተዳደር በሁለት ሳምንት ውስጥ ወይንም በተሰጠው የግዜ ገደብ መሰረት ዴፖርቴሽኑን በመቃወም ይግባኝ ማለት አለባችሁ ቀኑ የሚቆጥረው ደብዳቤው በወጣበት ሳይሆን ደብዳቤው እናንተ ጋ ደርሶ በተቀበላችሁበት ቀን ነው የሚቆጠርው ስለዚህ ሁልጊዜ የማስተዎቂያ ሰሌዳውን መመልከት አለባቸሁ ስላመለከታችሁ ዲፓርት አትሆኑም ማለት አይደለም ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ጉዳያችሁን እያየሁት ነው የሚል ደብዳቤ እስካልፃፈ ድረስ ጀርመን የመቆየት እድላችሁ ሙሉ ለሙሉ አልቋል ማለት አይደለም ስለዚህ በጠበቃችሁ በኩል አስቸኳይ የሆነ የይግባኝ ደብዳቤ እየታዬ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ከፍርድ ቤት መምጣት አለበት

### ትኩረት :-
እንዲዘገይ የተደረገው ይግባኛችሁ በፍርድ ቤት ውድቅ ከተደረገ የስድስት ወር ግዜ ከመጀመሪያው ውድቅ ከተደረገበት ግዜ ጀምሮ ቀኑ ይሮጣል ስለዚህ ጠንቃችሁ ግዜውን በመከታተል ባለሙያና ጠበቃችሁን በማማከር የግዜ ገደቡን ለማምለጥ መሞከር ነው

### ትኩረት:-
በምታመለክቱበት ግዜ ምክንያቶችን ዘርዘር አድርጋችሁ በተለይ በፊት በምትኖሩበት አገር የደረሰባችሁን በደልና ለምን ጥገኝነት እንደከለከላችሁ ወይንም ለምን እንደመጣችሁ እናንተን የሚገልፅ መርጃ ለጠበቃችሁ ማስረዳትና መግለፅ ይገባችኃል

በሽተኛ ወይንም የተለየ የጤና ችግር ካለባችሁ ከዶክተር ወይንም ከስነልቦና ባለሙያዎች ህመማችሁን የሚገልፅ ሰርቲፊኬት በማቅረብ ለጠበቃችሁ በመስጠት ጉዳያችሁ የተሻለ እንዲታይ ይሆናል

ይግባኝችሁ በጀርመን ፍርድ ቤት ታይቶ ውድቅ ከሆነ ለአውሮፓ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይቻላል እነዚህ ህደቶች ስታከናውኑ ጠበቃችሁን እያማከራችሁ መሆን አለበት

## በመጨረሻው ደቂቃ ዲፓርቴሽንን እንዴት መቆቋም ትችላላችሁ

ከዚህ በታች ያሉትን ሊንክ በማንበብ ዲፖርቴሽንን እንዴት መቆቋም እንደምትችሉ ስፍ ያለ ግንዛቤ ይሰጧችኃል

http://w2eu.info/germany.en/articles/germany-deportation .en.html
https://www.youtube.com/watch?v=g2Umb7MyDhw&feature=youtu.be
http://nodeportation.antira.info/abschiebungen-verhindern/

ይህ መመሪያ የተፃፈው በተባበሩት አውሮፓውያን "እንኳን ደህና መጣችሁ"በማለት የተመሰረቱ ከመቶ በላይ አክቴቢስት ከ2009ጀምሮ ጥገኝነትን ጠያቂዎችን እና ፈላሻዎችን ሲደግፍ ቆይተዋል

አንዳንዶቻችን በድንበር አካባቢዎች የሚደረግ ማስፍራራትና ዲፖርት ማድረግን ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል እንደዚሁም አውሮፖም የተወለዱት ለዚህ ችግር ተጠቂ ሆነዋል

የሰው ልጆች በይትኛውም አገር የመዘዋወር መብታቸው የተጠበቀ ስለሆነ በየትኛውም አለም የምንገኝ አክቲብስቶች ልንደግፍችው ይገባል

ይህ መመሪያለሁሉም ፈላሻ በተለይ የእጅ አሻራ ኖሮበት ከጀርመን ወደሌላ አገር ዲፖርት ለሚሆኑ መድረስ አለበት(በተለይ ጣልያን ሀንጋሪ ቡልጋሪያና ግሪክ)

ይህ የመመሪያ ቅጅ የተፅፈው ከነሀሴ 2017 ጀምሮ ሲሆን በየግዜው መሸሻል ተደርጎበታል ስለዚህ ማንበብና ዳውን ሎድ በማድረግ ሙሉን መመሪያ በቀጥታ ከዚህ ሊንክ ማግኘት ትችላላችሁ

http://w2eu.info/germany.en/articles/germany-dublin2.en.html
በተጨማሪ በተለያዩ ቋንቋዎች ማግኘት ትችላላችሁ
በተለይ በአረበኛ በእንግሊዝኛ በፋሪስ እናበፍሪንች
http://w2eu.info